# የስደተኛ ጠያቂዎች መረጃ

## 1. አጠቃላይ መረጃ:-

ከስደተኛ ጠያቂዎች ጋር የሚሰሩ የካናዳ መንግስት አካላት

- **የካናዳ የኢሚግሬሽን ስደተኞች እና ዜግነት( አይአርሲሲ)** (www.canada.ca/en/services/immigration-citizenship.html): (አይአርሲሲ) አይአርሲሲ በካናዳ ውስጥ የሚቀርበው የስደተኞች ጥያቄ ወደ ካናዳ ኢሚግሬሽን የስደተኞች ቦርድ (ኣይኣርቢ) እና የስደተኞች ጥበቃ ክፍል (አርፒዲ) ለመቅረብ ብቁ መሆን አለመሆኑን ይወስናል።
- **የካናዳ ድንበር አገልግሎት ኤጀንሲ (ሲቢኤስኤ)** (www.cbsa-asfc.gc.ca): ሲቢኤስኤ አገልግሎቶች በካናዳ የመግቢያ ወደብ (ማለትም አውሮፕላን ማረፊያ፣ የመሬት ድንበር ማቋረጫ ወይም የባህር ወደብ) ወይም ስደተኛ ጥያቄን ይወስናል። በአገር ውስጥ አስከባሪ ቢሮ ውስጥ ወደ የስደተኞች ጥበቃ ክፍል ለመመራት ይችላል።
- **የካናዳ የኢሚግሬሽን እና የስደተኞች ቦርድ (ኣይኣርቢ .)** (www.irb-cisr.gc.ca): ኣይኣርቢ የኢሚግሬሽን እና የስደተኛ ውሳኔዎችን የማድረግ ኃላፊነት ያለው ገለልተኛ አካል ነው።

## 2. ጠበቃ ወይም አማካሪ የመወከል መብት

እንደስደተኛ ጠያቂ በስደተኛ የይገባኛል ጥያቄ ሂደት ወቅት በራስዎ ወጪ አማካሪ (ጠበቃ ወይም ሌላ ባለሙያ ተወካይ) የመወከል መብት አልዎት። ለ ጠበቃ መክፈል ካልቻሉ፣ የክፍለ ሀገር ወይም ወረዳ ክልል የህግ ድጋፍ ቢሮ እርዳታ መጠየቅ ወይም ማመልከት ይችላሉ።

የካናዳ መንግስት ጠበቃ ወይም አማካሪ ቢጠቀሙም ባይጠቀሙም ሁሉንም ሰው በእኩልነት ይመለከታል። አማካሪ ወይም ጠበቃ ለመቅጠር ሰለመረጡ ማመልከቻዎ ልዩ ትኩረት ሊሰጠዉ ኣይችልም።

ጠበቃ ወይም አማካሪ ስለ መቅጠር መረጃ: www.canada.ca/en/immigration-refugees-citizenship/services/immigration-citizenship-representative.html።

**ማሳሰቢያ:** የአካባቢውን የስልክ ማውጫ ይመልከቱ ወይም ይህንን ሊንክ በመጠቀም የክልል እና የክልል የህግ ድጋፍ አገልግሎቶችን ድረ-ገጾች www.justice.gc.ca/eng/fund-fina/gov-gouv/aid-aide/index.html ን ይጎብኙ።

## 3. የስደተኛ ጥያቄዎን ለማቅረብ

### ሲቢኤስኤ

የመግቢያ ወደብ ላይ ሲደርሱ ለ ሲቢኤስኤ መኮንን በአካል ቀርበው የስደተኛ ጥያቄዎን መጠየቅ ይችላሉ።

አንድ ባለስልጣን የይገባኛል ጥያቄዎ ወደ የስደተኞች ጥበቃ ክፍል ለመቅረብ ብቁ መሆኑን ወዲያውኑ ሊወስን ካልቻለ፣ የይገባኛል ጥያቄ እውቅና ሰነድ ይሰጡዎታል። ይህ ጊዜያዊ ሰነድ ነው

- የስደተኛ ጥያቄ ማቅረቦትን ያረጋግጣል
- በጊዜያዊነት የፌዴራል ጤና ፕሮግራም አገልግሎቶች መሸፈንዎን ያሳያል
- ለማህበራዊ አገልግሎቶች ካመለከቱ ሊረዳዎ ይችላል.

**ለ ሲቢኤስኤ** የይገባኛል ጥያቄ ካቀረቡ እና የይገባኛል ጥያቄዎን በመስመር ላይ ወይም በኢንተርኔት ላይ እንዲያጠናቅቁ ይህንን አይአርሲሲ ፖርታል: portal-portail.apps.cic.gc.ca/signin?lang=en ይጠቀሙ።

በመስመር ላይ ወይም በኢንተርኔት የይገባኛል ጥያቄዎን ለመሙላት እርዳታ ለማግኘት ወደ www.canada.ca/en/immigration-refugees-citizenship/ services/application/application-forms-guides/guide-0192-cbsa- refugee-claims-ircc-portal.html ይመልከቱ። እንዲሁም የይገባኛል ጥያቄ መሰረት ቅጽ መሙላት ይኖርብዎታል። ይህንን ቅጽ ለ ኣይኣርቢ በፖስታ እንዲልኩ ወይም ወደ (አይራሲሲ) ፖርታል እንዲጭኑት ሲታዘዙ ይችላሉ (ለበለጠ መረጃ ክፍል 11 ይመልከቱ)። ተጨማሪ ነገሮች ካሉ **ሲቢኤሲኤ** ያሳውቅዎታል።

### አይአርሲሲ

ካናዳ ውስጥ ከሆኑ፣ በ አይራሲሲ ፖርታል በኩል በመስመር ላይ ወይም በኢንተርኔት የስደተኛ ጥበቃ ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ። የይገባኛል ጥያቄዎን በመስመር ላይ ለመሙላት እርዳታ ወደ እዚህ ማመልከቻ መመሪያ www.canada.ca/en/immigration-refugees-citizenship/services/ application/application-forms-guides/guide-0174-inland-refugee-claims-portal.html ይመልከቱ። የይገባኛል ጥያቄዎን በመስመር ላይ ወይም በኢንተርኔት ካስገቡ በኋላ:-

- የስደተኛ ይገባኛል ጥያቄ እውቅና ሰነድ ይሰጥዎታል።
- የእርስዎን ባዮሜትሪክስ (የጣት አሻራዎች እና ፎቶ) ለመሰብሰብ ቀጠሮ ለመያዝ አይራሲሲ ያነጋግርዎታል ቃለ መጠይቅ ላይ መገኘት አለብህ፣ ምናልባትም ሌላ ጊዜ ሊሆን ይችላል።

## 4. ጊዜያዊ የፌዴራል ጤና ፕሮግራም

በጊዜያዊ የፌደራል ጤና ፕሮግራም (**አይኤፍኤችፒ**) የካናዳ መንግስት ለአንዳንድ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ወይም ምርቶች ወጪ ይሸፍናል። የይገባኛል ጥያቄዎ ወይም የስደተኛ ጥበቃ የይገባኛል ጥያቄ ሰነድዎ (ክፍል 9 ይመልከቱ) ለ አይኤፍኤችፒ ሽፋን ብቁ መሆንዎን ያሳያል።

ሁሉም ብቁ የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢዎች በ **አይኤፍኤችፒ** ከተመዘገበ ከማንኛውም የጤና እንክብካቤ አቅራቢ በካናዳ ውስጥ በማንኛውም ቦታ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን እና ሃኪሞችን ማግኘት ይችላሉ። የጤና እንክብካቤ የተመዘገቡ ሃኪሞችን ዝርዝር በ https://ifhp.medaviebc.ca ላይ ይገኛል።

ከእነሱ ማንኛውንም አገልግሎት ከማግኘትዎ በፊት የጤና እንክብካቤ አቅራቢ በ **አይኤፍኤችፒ** መመዝገቡን ማረጋገጥ አለቦት። ትክክለኛ የይገባኛል ጥያቄ ወይም የስደተኛ ጥበቃ የይገባኛል ጥያቄ ሰነድ ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ በእያንዳንዱ ጉብኝት መቅረብ አለበት።

የትኞቹ ምርቶች እና አገልግሎቶች እንደሚሸፈኑ ለማወቅ ስለ **አይኤፍኤችፒ** ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.canada.ca/ifhp ወይም https://ifhp.medaviebc.ca ን ይጎብኙ።

## 5. የኢሚግሬሽን የሕክምና ምርመራ

እንደ ስደተኛ ጠያቂ በ30 ቀናት ውስጥ የግዴታ የህክምና ምርመራ ማድረግ አለቦት። የሚከፈለው በ **አይኤፍኤችፒ** ነው።

የተወሰኑ ዶክተሮች ብቻ እነዚህን የሕክምና ምርመራዎች ሊያደርጉ ይችላሉ. መመሪያዎች እና እነዚህን የሕክምና ምርመራዎች በእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር ወይም ግዛት **አይራሲሲ** ን ወክለው የሚሰሩ ዶክተሮች ዝርዝር አገናኝ በ **አይኤምኤ** 1017 የሕክምና ሪፖርት ቅጽ ላይ ቀርቧል።

Amharic | Amharique

ለህክምና ምርመራ ቀጠሮ ለመያዝ እባክዎን በዝርዝሩ ውስጥ ካሉ ዶክተር ጋር ቀጠሮ ይዝዉ ያነጋግሩ. በቀጠሮው ላይ የሚከተሉትን ሰነዶች ይዘው መምጣት አለብዎት።

- የ **አይኤምኤም** 1017 የሕክምና ሪፖርት ቅጽ እና
- የእርስዎን የይገባኛል ጥያቄ ወይም የስደተኛ ጥበቃ የይገባኛል ጥያቄ ሰነድ ይዝዉ መምጣት አለብዎት።

እባኮትን የመኖሪያ አድራሻዎን ወደ ሐኪም ቀጠሮ ይዘው ይምጡ

## 6. የስራ ፍቃድ እና የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር

በካናዳ በህጋዊ መንገድ ለመስራት የስራ ፍቃድ እና የሶሻል ኢንሹራንስ ቁጥር (**ኤሰ አይ ኤን**) ሊኖርዎት ይገባል።

ለማንኛውም ስራ ለመስራት በመስመር ላይ ወይም በኢንተርኔት የስደተኛ ጥያቄ ማመልከቻዎ (በ **አይአርሲሲ** ፖርታል በኩል) ያለክፍያ የስራ ፍቃድ መጠየቅ ይችላሉ። የሥራው ፍቃድ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሰራ  በስራ ፈቃድ ላይ ይገለጻል።

**አይአርሲሲ** የስራ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት፣ የሚከተሉት እርምጃዎች መከሰት አለባቸው።

- የይገባኛል ጥያቄዎ ብቁነት ላይ ውሳኔ መደረስ አለበት።
- የኢሚግሬሽን የህክምና ምርመራዎ መጠናቀቅ እና ማለፍም አለብዎት።
- ባዮሜትሪክስ (የጣት አሻራዎች እና ፎቶግራፎች) መወሰድ አለብዎት (ክፍል 8 ይመልከቱ)።

የኢሚግሬሽን የሕክምና ምርመራዎን ማጠናቀቅዎን የሚያረጋግጡት የ"IME" ቁጥር ወይም የኢሜዲካል መረጃ ሉህ ቅጂ ነው (ይህ ምርመራውን ከሚያካሂደው ዶክተር ሊጠየቅ ይችላል (ክፍል 4 ይመልከቱ))።

በስደተኛ የይገባኛል ጥያቄ ሂደት ወቅት የስራ ፈቃድ ካልጠየቁ፣ በመስመር ላይ www.canada.ca/en/services/immigration-citizenship.html. ላይ ማመልከት ይችላሉ።

**ማሳሰቢያ**:- የስራ ፈቃዱ አንዴ ከተሰጠ በኋላ በፖስታ ይላክልዎታል። አድራሻዎ ትክክል መሆኑን ያረጋግጡ በጣም አስፈላጊ ነው። አድራሻ ለመቀየር፣ እባክዎን የ **አይአርሲሲ** ድረ-ገጽ ይመልከቱ: secure.cic.gc.ca/enquiries-renseignements/canada-case-cas-eng.aspx እና "የ አድራሻ መረጃ ለውጥ" የሚለውን ይምረጡ። የስራ ፈቃድህን ስታገኝ ለሶሻል ኢንሹራንስ ቁጥር ማመልከት አለብህ። የይገባኛል ጥያቄዎን እውቅና ሰነድ እንደ **ኤሰ አይ ኤን** ማመልከቻዎ አካል አድርገው ማመልከት ይችላሉ። ይህንን በመስመር ላይ፣ በፖስታ ወይም በአካል ወደ አገልግሎት ካናዳ ማእከል  ሄደዉ ማመልከት ይችላሉ። የማመልከቻውን ሂደት በተመለከተ መረጃ በ www.canada.ca/en/employment-social-development/services/sin.html. ላይ ይገኛል። በአቅራቢያ ያለዉን አገልግሎት ካናዳ ማእከልን ለማግኘት ወደ 1 800 ኦ-ካናዳ (1-800-622-6232) ይደውሉ።

## 7. የትምህርት ቤት ምዝገባ ፈቃድ  ወይም የጥናት ፈቃድ

ከ18 አመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው የስደተኛ ጥያቄ ያቀረበ ወይም የጥገኝነት ጥያቄ ጠያቂ ልጅ በቅድመ ትምህርት ቤት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ (እስከ 12 ክፍል) ያለ የትምህርት ቤት ምዝገባ ፈቃድ መማር ይችላል። ትምህርት ቤት ለመመዝገብ የልጁ የይዉን ገባኛል ጥያቄ ወይም የስደተኛ ጥበቃ የይገባኛል ጥያቄ ሰነድ ያስፈልጋል።

በድህረ ሁለተኛ ደረጃ (ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ) ለመማር ለሚፈልጉ አመልካቾች ሁሉ **የትምህርት ቤት ምዝገባ ፈቃድ** ያስፈልጋል። በካናዳ በህጋዊ መንገድ ለመማር እና **የትምህርት ቤት ምዝገባ ፈቃድ**ከመሰጠቱ በፊት የኢሚግሬሽን የህክምና ምርመራ ፎርም ተሞልቶ ህክምናዉን ማለፍ ያስፈልጋል።

የጥናት ፈቃድ ወይም የትምህርት ቤት ምዝገባ ፈቃድ ማመልከቻው በ www.canada.ca/ en/services/immigration-citizenship.html ላይ ይገኛል። ለስደተኛ ጠያቂዎች ለጥናት ፈቃድ ለማመልከት ምንም ክፍያ የለም።

ለጥናት ፈቃድ ወይም **ለትምህርት ቤት ምዝገባ** ለማመልከት የሚከተሉት ሰነዶች ያስፈልጋሉ:

- የይገባኛል ጥያቄ ወይም **የስደተኞች ጥበቃ የይገባኛል ጥያቄ ሰነድ ቅጂ** (ክፍል 9 ይመልከቱ)
- ከታወቀ የትምህርት ቤት ተቋም የመቀበል ማረጋገጫ

በኩቤክ ግዛት ውስጥ ለመማር፣ በሚኒስቴር ደ l'ኢሚግሬሽን የተሰጠ የምስክር ወረቀት (**ሲኤአ**)፣ de la Francisation et de l'Intégration (**ሚፊ**)። እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ለበለጠ መረጃ: https://www.quebec.ca/en/education/study-quebec. ይጎብኙ።

## 8. ባዮሜትሪክስ (የጣት አሻራዎች እና ፎቶግራፎች)

የስደተኛ ይገባኛል ጥያቄዎን በመግቢያ ወደብ ላይ ካደረጉ፣ የኛ ሲቢኤስኤመኮንን የእርስዎን ባዮሜትሪክስ ወስዶ የማንነት ማረጋገጫ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶችን ይሰበስባል። እርስዎም የሚከተሉትን ያደርጋሉ:-

- የብቃት ቃለ መጠይቁን ያጠናቅቁ፣ ወይም
- ባለሥልጣኑ ወደ ካናዳ እንድትገቡ እና ለተጨማሪ ምርመራ ወደ አይአርሲሲ ወይም ሲቢኤሰኤ ቢሮ እንድትመለሱ ቀን እና ሰዓት ሊወስን ይችላል። በሲቢኤሰኤ ኦፊሰር ከታዘዙ የስደተኛ ጥያቄን በመስመር ላይ በ አይአርሲሲ ፖርታል ከቃለ መጠይቁ ቀን በፊት ማስገባት ይችላሉ።

አስቀድመው ካናዳ ውስጥ ከገቡ እና የስደተኛ ጥያቄን በመስመር ላይ በ አይአርሲሲ ፖርታል በኩል እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።

- የባዮሜትሪክስ ሰነድ ለማቅረብ ለ አይአርሲሲ ቢሮ ሪፖርት አድርግ
- የማንነትዎን ማረጋገጫ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶችን ያስገቡ ፣
- ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ቆይተው በኋላ ተመለሱ፤ እና
- ዕድሜያቸው ከ14 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶዎችን ወደ ባዮሜትሪክ ቀጠሮዎ ይዘው ይምጡ (ዕድሜያቸው 14 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ፎቶዎችን ማምጣት አያስፈልግም)።

## 9. በመግቢያ ወደብ ወይም ጠረፍ ቃለ መጠይቅ ታደርጋላችሁ

በቃለ መጠይቅዎ አንድ መኮንን እነዚያህን ያደርጋል

- የይገባኛል ጥያቄዎ ብቁ ከሆነ የይገባኛል ጥያቄዎን ወደ የስደተኞች ጥበቃ ክፍል (**አርፒዲ**) ወደ አይአርቢ ይልክልዎታል።
- የይገባኛል ጥያቄዎ ብቁ ከሆነ የስደተኛ ጥበቃ የይገባኛል ጥያቄ ሰነድ (**ራፒሲዲ**) ይሰጣታል። (ከዚህ በታች ይመልከቱ)
- የመባረር ወይም የማስወገድ ትእዛዝ መስጠት:-
  - ↳ L የይገባኛል ጥያቄዎ ወደ አይአርቢ ለመቅረብ ብቁ ከሆነ የማስወገድ ትዕዛዙ ጊዜያዊ ይሆናል (ተግባራዊ አይሆንም)፣ በ በአይአርቢ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ።
  - ↳ L የይገባኛል ጥያቄዎ ብቁ ካልሆነ የማስወገድ ትዕዛዙ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል።
  - ↳ L ስለ የማስወገድ ትዕዛዞች ለበለጠ፣ ክፍል 12ን ይመልከቱ።

- የይገባኛል ጥያቄዎ ብቁ ከሆነ ስለ **አይአርቢ** ሂደት መረጃ ይሰጥዎታል።

**የይገባኛል ጥያቄዎ ብቁ ሆኖ ከተገኘ እና ወደ አይአርቢ** ከተላከ፣ በ **በአይአርቢ** የስደተኞች ጥበቃ ክፍል ችሎትዎ ላይ መገኘት አለቦት። ችሎቱ የሚሰማበትን ቀን እና ቦታ ሌላ ጊዜ አይአርቢ ያሳውቅዎታል።

- የይገባኛል ጥያቄዎ ብቁ እንዳልሆነ ከተረጋገጠ ወይም አሉታዊ ውሳኔ **በ በአይአርቢ** ላይ ከተሰጠ፣ ስለቀጣዮቹ እርምጃዎች ይነገረዎታል እና እርስዎም ይችላሉ

የይገባኛል ጥያቄዎ ብቁ ሆኖ ከተገኘ እና ወደ **አይአርቢ** ከተላከ፣ በ **አይአርቢ** የስደተኞች ጥበቃ ክፍል ችሎትዎ ላይ መገኘት አለቦት። ችሎቱ የሚሰማበትን ቀን እና ቦታ ለማሳወቅ አይአርቢ በሌላ ቀን ያነጋግርዎታል።

**ራፒሲዲ** የካናዳ የስደተኛ ጠያቂ እንደመሆኖ የይገባኛል ጥያቄ እውቅናን እንደ ዋና መታወቂያ ሰነድዎ ይተካል።

- የይገባኛል ጥያቄዎ ወደ **አይአርቢ**እንደተላከ ያሳያል
- አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ሊረዳዎ ይችላል እና
- **በጊዜያዊ የፌደራል የጤና ፕሮግራም መሸፈንዎን ያሳያል።**

## 10. የእውቂያ መረጃ ወይም የመገኛ አድራሻ

ሁሉም የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢዎች ማንኛውንም የአድራሻ ወይም ስልክ የመገኛ አድራሻ ለውጦች ለ **አይአርሲሲ** ማሳወቅ አለባቸው። ሁሉንም ነገር በ **አይአርሲሲ** ዌብፎርም ማጠናቀቅ ይቻላል: secure.cic.gc.ca/enquiries-renseignements/canada- case-cas-eng.aspx "የእውቂያ መረጃ ለውጥ" የሚለውን በመምረጥ።

**ማሳሰቢያ**: አንዴ የይገባኛል ጥያቄዎ ወደ አይአርቢ ከተላከ፣በግንኙነት መረጃ ላይ ስላለው ማንኛውም ለውጥ ለ **አይአርቢ** መናገር አለብህ። ይህንን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል መመሪያዎች በ **አይአርቢ** የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ መመሪያ ውስጥ ተካትተዋል: www.irb-cisr.gc.ca/Eng/RefClaDem/Pages/ClaDemGuide.aspx.

## 11. የኢሚግሬሽን እና የስደተኞች ቦርድ የይገባኛል ጥያቄ ሰነድ

ሁሉም ብቁ የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢዎች ወደ አይአርቢ ይገባኛል ጥያቄ ሰነድ ይመራሉ ። ኪቱ ወይም ሰነዱ በአይአርቢ ውስጥ ለችሎት እንዴት መዘጋጀት እንደሚቻል ጠቃሚ መረጃ ይዟል።

ይህ ስብስብ ወይም ሰነድ የሚከተሉትን ያካትታል:

**የይገባኛል ጥያቄ ቅጽ**

ይህ ሰነድ ለሁሉም የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢዎች ማቅረብ ግዴታ ነው። እያንዳንዱ ግለሰብ የየራሱ የይገባኛል ጥያቄ መሰረታዊ ቅፅ ሊኖረው ይገባል።

በመግቢያ ወደብ ላይ የስደተኛ ጥያቄ ካቀረቡ: የይገባኛል ጥያቄ መሰረት ቅጹን በ15 ቀናት ውስጥ ወይም **በሲቢኤስኤ** ባዘዘው ጊዜ ውስጥ ለ አይአርቢ ማቅረብ አለበት። የተሞላውን የይገባኛል ጥያቄ ቅጽ (**ቢኦሲ**ቅጽ) በሰዓቱ ካላቀረቡ፣ የስደተኞች ጥበቃ ክፍል (አርፒዲ) የይገባኛል ጥያቄዎ በሪሰህ ፈቃድ ወይም በፈቃደኝነት እንደተውከዉ ሊገልጽ ይችላል ወይም ያስታውቃል።

የይገባኛል ጥያቄዎን በመስመር ላይ በ IRCC ፖርታል በኩል ካቀረቡ፣ የይገባኛል ጥያቄ መሰረት ቅጽ እንደ ድጋፍ ሰነድ መያያዝ አለበት።

**ማሳሰቢያ**: የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢው አማካሪዎቻቸው ወይም ጠበቆቻቸው የይገባኛል ጥያቄውን መሰረት በጊዜው ለ አይአርቢ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

**የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ መመሪያ**

የይገባኛል ጥያቄ ሰጪው መመሪያ የ **አይአርቢ** የስደተኞች ጥበቃ ክፍል ሂደትን ያብራራል እና በ irb.gc.ca/en/refugee-claims/Pages/ClaDemGuide.aspx ላይ ይገኛል።

**ችሎት ላይ ለመገኘት ጠቃሚ መመሪያዎች**

እነዚህ መመሪያዎች ችሎት ላይ ለመገኘት ጠቃሚ መመሪያዎች እና ተጨማሪ የስደተኛ የይገባኛል ጥያቄ ሂደት መረጃን በተመለከተ ጠቃሚ መረጃ ኣሏቸዉ።

**የክልል እና የክልል የህግ እርዳታ የእውቂያ መረጃ**

ለህግ አማካሪ ወይም ለጠበቃ መክፈል ካልቻሉ የህጋዊ እርዳታ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ጠበቃ ወይም የአማካሪ አድራሻ መረጃ ቅጽ (አይአርቢ/ሲአይኤስአር101.02):**

የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢው (አማካሪ ወይም ጠበቃ ከያዘ አግባብ ባለው አካል አባል የሆነ እና ጥሩ ችሎታ ያለው) በተጨማሪ የአማካሪ አድራሻ መረጃ ቅጽ በአማካሪዉ ተሞልቶ ለ አይአርቢ መቅረብ አለበት: (irb-cisr.gc.ca/en/forms/Documents/ IrbCisr10102_e.pdf)።

የጠበቃ ምክር ክፍያዎች በክልል ወይም በግዛት የህግ እርዳታ አገልግሎት የሚከፈሉ ከሆነ ተመሳሳይ ነው።

የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢው ጠበቃ በለወጠ ቁጥር አዲስ የአማካሪ ወይም የጠበቃ አድራሻ መረጃ ቅጽ ተሞልቶ ለ **አይአርቢ** መቅረብ አለበት።

**ያለክፍያ እርስዎን የሚወክል አማካሪ የውክልና ቅጽ መሙላት አለበት። (አይአርቢ/ሲአይኤስአር 101.03):**

አማካሪዎ የሚከፈላቸው ካልሆነ፣ የውክልና ማስታወቂያውን ያለክፍያ ቅጽ irb.gc.ca/en/forms/Documents/ IrbCisr10103_e.pdf መሙላት እና ለ **አይአርቢ** ማቅረብ አለባቸው።

አማካሪን ከቀጠሩ፣ ነገር ግን አይአርቢ የ **አይአርቢ/ሲአይኤስአር** 101.02 ወይም **አይአርቢ/ሲአይኤስአር** 101.03 ቅፅን ካልተቀበለ፣ወይም ቅጹን ካላገኘ አማካሪዎ እርስዎን ወክለው በ **አይአርቢ** ስብሰባዎች ላይ እንዲሰሩ አይፈቀድለትም።

## 12. የማስወገጃ ትዕዛዞች

ባጠቃላይ አነጋገር፣ አብዛኞቹ ስደተኞች ጠያቂዎች በቃለ መጠይቁ ወቅት የማስወገጃ ትእዛዝ ይሰጣል። የማስወገጃ ትእዛዝ በአንተ ላይ ከተሰጠ፣ ቅጂው ይሰጥሃል።

የይገባኛል ጥያቄዎ ወደ የስደተኞች ጥበቃ ክፍል ለመቅረብ ብቁ መሆኑን ከተወሰነ፡ በጥያቄዎ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በካናዳ ውስጥ ሊቆዩ ይችላሉ። የይገባኛል ጥያቄዎ በስደተኞች ጥበቃ ክፍል ተቀባይነት ካገኘ፣ የማስወገጃ ትእዛዝዎ ተፈጻሚነት የለውም እና ለቋሚ መኖሪያነት ማመልከት ይችላሉ።

ነገር ግን የይገባኛል ጥያቄዎ ብቁ ሆኖ ካልተገኘ፣ ወይም እርስዎ በፈቃደኝነት በይገባኛል ጥያቄዎ ጉዳይ መቀጠል ካልፈለጉ ፣ ወይም የስደተኞች ጥበቃ ክፍል በእርስዎ የይገባኛል ጥያቄ ላይ አሉታዊ ውሳኔ ወይም ተቀባይነት ካላገኘ የማስወገጃ ትእዛዙ ተግባራዊ ይሆናል።

የመልቀቂያ ትእዛዝ ከተሰጠህ፣ የመልቀቂያ ትዕዛዙ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ምክር ይሰጥሃል ወይም ይነገርሃል ፣ እና በ30 ቀናት ውስጥ ከካናዳ መውጣት አለብህ የሚል ምክር ይሰጥሃል፣ወይም ይነገርሃል ። ከካናዳ ከመውጣትዎ በፊት፣ መሄድዎን የማረጋገጥ ዝግጅት እንዲያደርጉ **ለሲቢኤስኤ** ቢሮ ከታቀደዉ የመሄጃ ግዜ በፊት ማሳወቅ አለብዎት። በ30 ቀናት ውስጥ ከካናዳ ካልወጡ፣ ወይም **ከሲቢኤስኤ** ጋር ከአገር ስለመውጣት ጉዳይ ካልተስማሙ፣ የመነሳትዎ ማረጋገጫ ተረጋገጠ፣ የመነሻ ትዕዛዙ ወዲያውኑ **የመባረር ትእዛዝ ይሆናል**።

## 13. የኮቪድ-19 መረጃ

በዚህ ጊዜ ውስጥ እንዴት ደህንነትን መጠበቅ እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት እባክዎን የካናዳ የህዝብ ጤና ኤጀንሲን በኮቪድ-19 ድህረ ገጽ ላይ ይመልከቱ፡ . ይህ ድህረ ገጽ ኮቪድ-19ን ለመረዳት እንዲረዳዎ በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

---

ስለ ሌሎች የኢሚግሬሽን፣ የስደተኞች እና የዜግነት ካናዳ (አይአርሲሲ) ህትመቶች መረጃ ለማግኘት፡ ይጎብኙ።

በተጠየቅ ጊዜ የተለያዩ አማራጮች ማግኘት ይቻላል።

Also available in English under the title: Information Pamphlet for Refugee Claimants.

በመስመር ላይ ይጎብኙን።
ድር ጣቢያ ኢንተርኔት፡ ircc.canada.ca
ፌስቡክ፡ www.facebook.com/CitCanada
ዩቲዩብ ቻናል፡ www.YouTube.com/CitImmCanada
ትዊተር: @CitImmCanada

© ግርማዊ ንጉሱ በካናዳ ፣ በዜግነት እና ኢሚግሬሽን ሚኒስትር የተወከለው፣ 2024።

Cat. No. Ci44-25/2024Amh-PDF ISBN-978-0-660-71293-2 IRCC-3759-03-2024